እውነታ ጽሁፍ ወረቀት

# የቪክቶሪያ መንጃ ፈቃድዎን እንዴት እንደሚያወጡ

## የውጭ አገር ፈቃድ ለያዙ መመሪያ

ፈቃድ አግንኝቶ በቪክቶሪያ ውስጥ ለመንዳት፤ የመንገድ ደንቦችን ተረድተው የመኪና ደህንነትን መቆጣጠር ስለመቻልዎ የቪክሮድ/ VicRoads መርካት አለበት።

### የጊዜያዊ ቪዛ ለያዙ

በጊዜያዊ ቪዛ ቪክቶሪያ ውስጥ ከሆኑ፣ በውጭ አገር የመንጃ ፈቃድዎ ላልተወሰነ ጊዜ መንዳት ይችሉ ይሆናል (ወቅታዊና ጊዜው ያላለፈበት መሆን አለበት)። የውጭ አገር የመንጃ ፈቃድዎ በእንግሊዝኛ መሆን አለበት (ወይም በእንግሊዝኛ የተተረጎመን ወይም የዓለም አቀፍ የመንጃ ፈቃድን አብሮ ማያያዝ)። ለቪክቶሪያ ፈቃድ ከጠየቁ፣ የሚፈለጉትን ፈተናዎች ካለፉ በኋላ የቪክቶሪያ መንጃ ፈቃድ ይሰጣል፣ ከዚያ በኋላ ለመንዳት የውጭ አገር መንጃ ፈቃድዎ ዋጋ አይኖረውም።

### ቋሚ ነዋሪዎች

በቋሚ ነዋሪነት ቪዛ ቪክቶሪያ ውስጥ ከሆኑ፣ በውጭ አገር የመንጃ ፈቃድዎ መንዳት የሚችሉት (ወቅታዊና ጊዜው ያላለፈበት መሆን አለበት) ይህም:

- አውስትራሊያ መጀመሪያ ከገቡበት ቀን ጀምሮ ለስድስት ወራት (የቋሚ ነዋሪነት ቪዛ የተሰጠው አውስትራሊያ ከመግባትዎ በፊት ከሆነ); ወይም
- የቋሚ ነዋሪነት ቪዛ ከተሰጥዎት በኋላ ለስድስት ወራት (የቋሚ ነዋሪነት ቪዛ የተሰጥዎት አውስትራሊያ ውስጥ ከሆነ)።

የውጭ አገር የመንጃ ፈቃድዎ በእንግሊዝኛ መሆን አለበት (ወይም በእንግሊዝኛ የተተረጎመን ወይም የዓለም አቀፍ የመንጃ ፈቃድን አብሮ ማያያዝ)። የስድስት ወራት ጊዜ ካለፈ በኋላ መንዳቱን ለመቀጠል ከፈለጉ የቪክቶሮያ መንጃ ፈቃድ ያስፈልግዎታል።

**የቪክቶሪያ መንጃ ፈቃድ ለማግኘት እድሜዎ 18 ዓመት መሆን አለበት።**

### የቪክቶሪያ መንጃ ፈቃድዎን ስለማውጣት

አንዳንድ አገሮች እንደ አውስትራሊያ ተመሳሳይ የመንጃ ፈቃድ ደረጃ አላቸው። የውጭ አገር መንጃ ፈቃድዎን ወደ ቪክቶሪያ መንጃ ፈቃድ ያለ ፈተና መቀየር ሲችሉ፤ ያለዎት መንጃ ፈቃድ ወቅታዊ ከሆነ ወይም ከአምስት ዓመት በላይ ጊዜው ያላለፈበት ከሆነ ነው። የርስዎ አገር በዚህ ስም ዝርዝር ውስጥ ከሆነ ለማየት ይህን መጨን: vicroads.vic.gov.au/OverseasDriversLicences

የቪክቶሪያ መንጃ ፈቃድ እንዲሰጥዎ ቀጠሮ ለማቀናጀት በስልክ 13 11 71 መደወል ወይም ወደ ቪክሮድ/ VicRoads ደንበኛ አገልግሎት ማእከል በአካል ሂዶ ማቀናጀት ነው።

የርስዎ መንጃ ፈቃድ በተዘረዘሩት አገሮች ዝርዝር ላይ ከሌለ የሚከተለውን ፈተና ማለፍ አለብዎ:

- ስለ መንገድ ላይ ደንቦች ያለህን እውቀት በኮምፒውተር ተደርጎ ፈተና፣ እና
- በኮምፒውተር ተደርጎ ለአደጋ ግንዛቤ ችሎታ ፈተና/ Hazard Perception Test, እና
- በመንገድ ላይ አነዳድ ፈተና።

እነዚህ ፈተናዎች ሁሉ የሚካሄዱት በቪክሮድ ደንበኛ አገልግሎት ማእከል ላይ ስለሆነ ቀደም ብሎ ቀጠሮ መቀናጀት አለበት። ቀጣዩን ፈተና ከመውሰድዎ በፊት ለእያንዳንዱ ፈተና ማለፍ አለብዎ። የፈተና ውጤቱ ለ12 ወራት ህጋዊ ተቀባይነት ይኖረዋል። በዚህ ጊዜ ውስጥ የመንጃ ፈቃድ ካልተሰጠ አዲስ ፈተና ማካሄድ ያስፈልጋል።

### የመንጃ ፈቃድ ትርጉም

ዓለም አቀፍ የመንጃ ፈቃድ ከተተረጎመ ተቀባይነት ይኖረዋል ይሁን እንጂ ከውጭ አገር የመንጃ ፈቃድ ጋር መቅረብ አለበት።

ዓለም አቀፍ የመንጃ ፈቃድ ከሌለዎት እና የርስዎ መንጃ ፈቃድ ከእንግሊዝኛ ባሻገር በሌላ ቋንቋ ከሆነ ታዲያ በእንግሊዝኛ ተተርጉሞ አብሮ መያያዝ አለበት። የማስተርጎሚያው ወጪ የርስዎ ሀላፊነት ነው።

በሚከተሉት የተጠናቀቀን ትርጉም ብቻ ቪክሮድ/VicRoads ይቀበላል:

- በ NAATI ተቀባይነት ያገኘ ተርጓሚ (ማንኛውም ደረጃ/ level)፣ ወይም
- በአውስትራሊያ ያለ ተክክለኛ ቆንሱላ፣ ወይም
- ከመጣበት አገር ህጋዊ የሆነ ትርጉም።

የመንጃ ፈቃድ ከሌለዎት ዋናውን ወይም በምስክርነት የተረጋገጠ ቅጅ ደብዳቤን ከሚከተለው ማቅረብ ይችላሉ:

- የርስዎን መንጃ ፈቃድ ዝርዝር ሁኔታ የሚገልጽ ከመንጃ ፈቃድ አቅራቢ ባለሥልጣን፣ ወይም
- ከአገርዎ የመንጃ ፈቃድ አቅራቢ ባለሥልጣን ጋር አድርጎ ከቆንሱል ስለርስዎ መንጃ ፈቃድ ዝርዝር ሁኔታ የተሰጠ መግለጫ

## ለመንጃ ፈቃድ ፈተናዎች

**ፈተናዎች ስለማስቀጠር**

- በስልክ 13 11 71 መደወል
- ቀጠሮ በሚያቀናጁበት ጊዜ ለፈተናው መክፈል አለብዎ
- ፈተናው በቋንቋዎ የማይቀርብ ከሆነና እንግሊዝኛ እንዲረዳዎ እርዳታ የሚፈልጉ ከሆነ ቪክሮድ ያለክፍያ በነጻ አስተርጓሚ ያቀርባል። ከአስተርጓሚ ጋር ፈተና ለማቀናጀት ወደ ቪክሮድ/ VicRoads ደንበኛ አገልግሎት ማእከል ሂዶ ማነጋገር።
- ለርስዎ ፈተና ምን ማምጣት እንዳለብዎ የደንበኛ አገልግሎት ማእከል ሀላፊ ይነግርዎታል

**በፈተናዎች ላይ ስለመገኘት**

- ፈተናው ከሚጀመርበት ጊዜ አስር ደቂቃ ቀደም ብሎ መድረስ
- ለፈተና ያስፈልጋል ተብሎ የተነገረዎን ሁሉንም ማምጣት
- የውጭ አገር መንጃ ፈቃድዎንና አስፈላጊ ከሆነም ትርጉሙን ማምጣት (የመንጃ ፈቃድ ትርጉም ክፍልን ማየት)
- በቀጠሮ ጊዜ ከዘገዩ ወይም ትክክለኛ ሰነዶችን ካላቀረቡ በፈተናው ላይ መቀመጥ አይችሉም

## በኮምፑውተር ተደርጎ ስለ መንገድ ደንቦች እውቀት ፈተና

ለፈተናው ዝግጅት ለማድረግ በመንገድ ላይ ለብቻ መንዳት የሚለውን ትንሽ መጽሐፍ ማንበብና ማወቅ ሲኖርብዎ ይህም በድረገጽ **vicroads.vic.gov.au** ላይ ማየት ይችላሉ። ትንሹ መጽሐፍ በእንግሊዝኛ፣ በቻይና (ማንዳሪን)፣ በቬትናሚስ፣ በቱርክኛ እና በአረብኛ ቋንቋ ቀርቧል።

በሚከተሉት ቋንቋዎች ፈተና ይቀርባል:

| | | |
|---|---|---|
| Albanian/አልባንኛ | Macedonian/ ማሰዶኒያ | Somali/ሱማልኛ |
| Arabic/አረብኛ | Persian/ፐርዢያ | Spanish/ስፓኒሽ |
| Cambodian/ ጋምቦዲያ | Russian/ራሽኛ | Turkish/ቱርኪሽ |
| Chinese/ቻይና | Serbian/ሰርቢያን | Vietnamese/ ቬትናሚስ |
| English/እንግሊዝኛ | Sinhalese/ሲንሃለሰ | |

በድረገጽ **vicroads.vic.gov.au** ላይ በእንግሊዝኛ መለማመልድ ይችላሉ።

### የአነዳድ እውቀት ፈተና:

- በመንገድ ደንቦች ያለዎት እውቀትና እንደ ሹፌር መሆን መጠን ስለሚኖርዎ ሃላፊነት ሲገመገም ይህም በመንገድ ላይ ለብቻ መንዳት በሚለው ትንሽ መጽሐፍ ላይ መሰረት ያደርጋል።
- 32 ጥያቄዎች እንዳለውና ፈተና ለማለፍ 78% ወይም በላይ ነጥብ ማግኘት አለብዎ

## በኮምፑውተር ተደርጎ አደጋን የመገንዘብ ችሎታ ፈተና

### የአደጋ ግንዛቤ ችሎታ ፈተና:

- በተለያዩ የትራፊክ ሁኔታዎች ላይ ማለት እንደ ለሌላ ተሽከርካሪዎች፣ እግረኞችና ብስክሌተኛ መገንዘብና እርምጃ መውሰድ ስለመቻልዎ ያጣራል
- በሹፌር አመለካከት የተውሰደ አጭር ቪዲዮ አለው። ታዲያ ሹፌር ከሆኑ መቸ እርምጃ መውሰድ እንዳለብዎ ያመለክታሉ (ለምሳሌ፡ ቀስ ለማለት ወይም ለመታጠፍ ሲጀመር)
- የሰጡት ምላሽ ካለው ደህንነት ጋር ይታያል
- ፈተናውን ለማጠናቀቅ 45 ደቂቃዎች ይኖርዎታል
- ለአደጋ ግንዛቤ ችሎታ ፈተና ከዚህ በላይ ካሉት ቋንቋዎች ውስጥ በአንደኛው መውሰድ ይችላሉ

## በመንገድ ላይ አነዳድ ፈተና

እርስዎ ደህንነቱ በተጠበቀ መንዳት ስለመቻልዎ ለማወቅ የአነዳድ ፈተናው ይረዳል። ማድረግ ያለብዎ:

- ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ መንዳት
- በቀላሉ መኪናውን መቆጣጠር
- የመንገድ ደንቦችን መከተል
- ከሌላ መንገድ ተጠቃሚዎች ጋር መተባበር

### የአነዳድ ፈተና:

- በቅድመ አነዳድ ፍተሻ የተመሰረተና ለአነዳድ ሁለት ደረጃዎች አሉ
- የመጀመሪያ አነዳድ ደረጃ ካለፉ ብቻ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ይገባሉ
- የመጀመሪያ አነዳድ ደረጃ ለ10 ደቂቃዎች ቀለል ያለ የትራፊክ መጨናነቅ ባለበት መንዳት ይሆናል። የሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ለ20 ደቂቃዎች ብዛት የትራፊክ መጨናነቅ ባለበት ሁኔታ ላይ መንዳት ነው

### ከርስዎ ጋር ማምጣት ስለሚኖርብዎ ማረጋገጥ:

- የቀጠሮ ማስያዣ ቁጥርዎን
- የውጭ አገር መንጃ ፈቃድዎንና ካስፈለገ ትርጉሙን (የመንጃ ፈቃድ ትርጉም ክፍልን ማየት)
- በመንገድ ላይ መጠቀም/ roadworthy የሚቻል መኪና (ቪክሮድስ. VicRoads ለመኪናዎች ምርመራ አያቀርብም)
- ለመንጃ ፈቃድ ክፍያ ማካሄድ

## ከአነዳድ ፈተና በኋላ

ፈተና ማለፍ ወይም አለማለፍዎን በመንጃ ፈቃድ ሀላፊው በኩል አስተያየት ይሰጥዎታል።

### በመንገድ ላይ የአነዳድ ፈተናን ሲያልፉ

ለመንጃ ፈቃድዎ የሚሆን ፎቶ ለመውሰድ ወደ ፎቶ ማንሻው ቦታ ይላካሉ። የመንጃ ፈቃድዎ በአንድ ሳምንት ውስጥ በፖስታ በኩል ይደርሳል። ለመንጃ ፈቃድ የከፈሉበት ደረሰኝ ስለሚሰጥዎ ታዲያ አዲሱ የመንጃ ፈቃድዎ እስከሚደርስ ለመንዳት ይህን መጠቀም ይችላሉ።

**የበለጠ መረጃ ለማግኘት በድረገጽ vicroads.vic.gov.au ላይ መጎብኘት ወይም በስልክ 13 11 71 መደወል ወይም ወደ ቪክሮድ/VicRoads የደንበኛ አገልግሎት ማእከል በአካል መሄድ ነው።**

*በዚህ እውነታ ጽሁፍ ወረቀት ውስጥ የቀረበው መረጃ በሚታተምበት ጊዜ ትክክል እንደሆነና ከዚያም ሊቀየር ይችላል።*

VRPIN02900 How to get your Victorian Driver Licence – Amharic Authorised by VicRoads, 60 Denmark Street, Kew, 3101

keeping victorians connected